“We orbit around the spaces!”

ስለ ሀገሮች አጫጭር ታሪክ

1. ግብፅ (Egypt):

- በጋዛሰርድ፣ በእስራኤል፣ በሊቢያ፣ በሱዳን፣ በሜዲትራንያን እና በቀይ ባህር የተከበበች አፍሪካዊ ሀገር ነች።
- ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3100 ዓ.ዓ እንደተመሰረተች ታሪክ ይነግረናል። ይህም በዓለማችን ቀዳሚ ህዝቦች ያደርጋቸዋል።
- የግብፅ ስልጣኔ የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1350 ዓ.ዓ ላይ ነው።
- ግብፅ ፓፒረስ የሚባል ለመፃፉ የሚጠቀሙበት ቅጠል ሲሆን ፀሐፉ ደግሞ ሄሮግሊፊክስ ይባላል።
- ጥንታዊ ግብፆች በሒሳብ እና በሳይንስ ይታወቁ ነበር። እንዲሁም በህንፃ ግንባታ፣ በመድሀኒት፣ በቀን አቆጣጠር እና በሌሎች ልዮልዮ ፈጠራዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው።
- ለአሁኑ ስልጣኔያችን ጥንታዊ ግብፆች የፈጠሩልን ብዙ ብዙ ነገሮች አሉ። **ለምሳሌ፦** መስኖ፣ ወረቀት፣ ብዕር፣ ቁልፍ፣ ቅባቶች እና የጥርስ ሳሙና የሚጠቀሱ ናቸው።
- ንጉስ ፈርኦን ቤተ መቅደስ፣ ፒራሚዶች እና የተለያዮ በወቅቱ አስደናቂ የሆኑ ሀውልቶች ማሰራት ችሏል። በአሁኑ ጊዜ 130 የሚሆኑ ፒራሚዶች በግብፅ ይገኛሉ።
- ዘመናዊ ግብፆች ብቅ ማለት የጀመሩት በ1944 ዓ.ም ላይ ነው።

2. ቻይና (China):

- ከክርስቶስ ልደት በፊት 2070 ቻይና ተመሰረተች።
- ጥንታዊ እና ረዥም የዘመናዊነት ታሪክ ያላት የእስያ አህጉር ቀዳሚ ሀገር ናት።
- በጥንቷ ቻይና ግብር ይከፈል ነበር የህግ የበላይነትም ነበር።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ሻይን የጠጡ ሰዎች ቻይናውያን ናቸው። የሻይ ቅጠልን በመጀመሪያ ለመድሀኒትነት ይጠቀሙት ነበር ከጊዜ በኋላ ግን የእለተእለት መጠጥ ተደርጓል።
- በ2002 ዓም 2400 ዓመት እድሜ ያለው የሾርባ ሳህን በቁፋሮ ተገኝቷል።
- በአለማችን ብዙ ህዝብ ያላት ቀዳሚ ሀገር ናት።
- በዓለም በትልቅነቷ 4 ተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት።
- ቻይና 14 ሀገራት ጎረቤቶቿ ናቸው።
- የቻይና ፊደል ከ 8000 በላይ ሲሆኑ እስከ 13 አመት ያሉ ልጆች 3000 የሚሆኑትን ማንበብ እና መፃፍ ይችላሉ።
- የቻይናውያን አዲስ አመት ለ 15 ቀናት በደማቅ ሁኔታ ሲከበር ይታያል።



“We orbit around the spaces!”



3. ህንድ (India):

- ህንድ በእስያ የምትገኝ በባህል እና በታሪክ የበለፀገች ሀገር ናት።
- በፓኪስታን በቻይና በኔፓል እና በባንግላዲሽ የተከበበች ስትሆን ዋና ከተማዋ ኒውዴልሂ ትባላለች ።
- ህንድ ውስጥ ሰዎች መኖር ጀምረዋል ተብሎ የሚታሰበው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 1500 ላይ ነው።
- በህዝብ ብዛቷ ደግሞ 2ተኛ ደረጃ ላይ ናት።
- ህንድ ለዓለም በሒሳብ በርካታ ነገሮች አበርክታለች እነዚህም:- አልጀብራ (Algebra)፣ ካልኩለስ (Calculus)፣ ትሪጎኖሜትሪ (Trignometry) እና ዜሮ ቁጥር (Zero number) የተፈለሰፈው በህንድ ነው።
- በህንድ ከክርስቶስ ልደት በፊት 700 ላይ የተሰራ ታክሻሺላ ዩኒቨርሲቲይ በአለማችን ጥንታዊ ዩኒቨርሲቲይ ነው።

4. ኢትዮጲያ (Ethiopia):

- ኢትዮጲያ ቀደምት ከሆኑት ሀገራት ውስጥ በቀዳሚነት የተቀመጠች ሀገር ናት።
- ኢትዮጲያ ውስጥ ስልጣኔ የጀመረው ከክ/ልደት በፊት 980 አካባቢ ነው።
- ቀደምት የሰው ቅሪተ አካል የተገኘው በኢትዮጲያ ሲሆን ከብዙ ሚልዮን አመታት በፊት ነው።
- ኢትዮጲያ በእደ-ጥበብ፣ በግብርና፣ በፍልስፍና፣ በክዋክብት እና በህክምና እውቀቶችን ለዓለም ያበረከተች ሀገር ናት።
- የራሷ የሆነ ቋንቋ፣ ፊደል እንዲሁም የቀን አቆጣጠር ያላት ባህሏን እና እምነቷን እስከዛሬ ጠብቃ ያቆየች ጥንታዊ ሀገር ናት።

5. ግሪክ (Greek):

- የግሪክ ታሪክ የሚጀምረው ከክልደት በፊት 800 ላይ ነው።
- ግሪክ ለዓለማችን መለወጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክታለች።
- ዘመናዊነት እንዲስፋፋ እና አዳዲስ ሀሳቦች እንዲፈጠሩ እንዲሁም የህንፃ አሰራሮች ማስተዋወቅ የቻለች ሀገር ናት።
- የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የስነ-ፁሑፍ፣ የህግ እና የፖለቲካ እድገትም ባለቤት ናት።
- የመጀመሪያ የኦሎምፒክ ጨዋታ የተደረገው ከክ/ልደት በፊት 776 ላይ ግሪክ ውስጥ ነው።
- ከአልባኒያ፣ ከሰሜን መቆዲንያ፣ ከ ቡልጋሪያ፣ ከቱርክ ጋር ትዋሰናች።
- የግሪክ 18 ቅርሶቿን በዩኔስኮ አስመዝግባለች።
- ሀገሪቷ 85/100 የሚሆነው ቦታዎቿ በተራራማ የተሸፈነ ነው።

6. ጃፓን (Japan):

- ጃፓን ከክ/ልደት በፊት 600 ላይ እንደተመሰረተች ይገመታል።
- በእስያ የምትገኝ ሀገር ስትሆን 4 ትላልቅ ደሴቶች እና ከ 6800 በላይ ትናንሽ ደሴቶች ተሰብስበው ጃፓንን ፈጥረዋታል።
- አርኪዮሎጂስቶች በዚያን ጊዜ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች አግኝተዋል።
- ጃፓን እየዘመነች የመጣችው በ 900 አመታት ውስጥ ነው።
- በአሁኑ ጊዜ ባህሏን ጠብቃ እየኖረች ያለች ዘመናዊ ሀገር ነች።



“We orbit around the spaces!”



7. ኢራን (Iran):

- ኢራን ከ/ክልደት በፊት 550 ላይ ተመሰረተች።
- በደቡብ ምዕራብ እስያ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት።
- የኢራን ቋንቋ ፐርሺያን ይባላል።
- የኢራን ሌላኛው ስሟ ፐርሺያ ነው ዋና ከተማዋ ደግሞ ትሒራን ትባላለች።
- በጥንት ጊዜ ስልጣኔ የነበራት ሀገር ስትሆን ከክ/ልደት በፊት 4000 ላይ ነው ስልጣኔን የጀመረችው።
- በነዳጅ እና በምንጣፍ ታዋቂ ሀገር ናት።
- በሚያማምሩ የምንጣፍ ስራዎቿ አለምን ለ 2000 አመታት ስታስደምም ኖራለች።
- 1 ጊዜ የእግር ኳስ ሜዳ የሚያክል ምንጣፍ ሰርታ ነበር።
- አንዳንድ ጊዜ ኢራናውያን በሚያስደንቅ ምንጣፋቸው ላይ አውቀው ስህተት ይሰራሉ። ይህም በአለም ከፈጣሪ በቀር ፍፁም ሰው የለም የሚለውን ለማሳየት ነው።

8. ፖርቹጋል (Porchugal):

- የብዙ ሺህ አመታት ባለታሪክ ስትሆን ስልጣኔ ተጀመረ የሚባለው 711 ዓ.ም ላይ ነው።
- ከአውሮፓ ሀገራት ረዥም ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን ዋና ከተማዋ ደግሞ ሊዝበን ትባላለች።
- ምዕራብ አውሮፓ የምትገኝ ሀገር ስትሆን በአትላንቲክ እና በሜዲትራንያን ባህር የተከበበች ናት።
- በአሳ ማስገር፣ በነዳጅ፣ በሲሚንቶ ምርት፣ በፐላስቲክ ምርት፣ በአልባሳት እንዲሁም በኢኮኖሚ ምርት ኢኮኖሚዋን የያዙልት ናቸው።

9. ፈረንሳይ (France):

- 476 ዓ.ም ላይ ተመሰረተች።
- በምዕራብ አውሮፓ ትልቋ ሀገር ናት።
- ዋና ከተማዋ ፓሪስ ስትሆን በ8 ሀገራት ትዋሰናለች።
- በ4ተኛው ክ/ዘመን ብቅ ማለት እንደጀመሩ ይነገራል። በ17ተኛው ክ/ዘመን ፈረንሳይ ታላቅ ሀገር ነበረች። በእስያ እና በአፍሪካ በርካታ ቀኝ የገዛቻቸው ሀገራት ነበሯት።

Thank you for reading!